# ኢትዮጵያውያንና ሥነምግባራዊ ባሕርይ?

ለዚህ መጣጥፍ መነሻ ይሆነኝ አቶ ይልማ በቀለ የተባሉ ጸሐፊ በተለያዩ ድረገጾች ላይ እንደ ፈረንጆቹ አቆጣጠር ከጥቅምት 12 ቀን 2012 ጀምሮ "The Ethiopians and Moral Conduct" በሚል ርዕስ ላቀለሙት ድርሰት ምላሽና የማብራሪያ ጥያቄዎች ወደፊት ለማለት ስል ነው።

አቶ ይልማ  በፈረንጆቹ ቋንቋ እንድናነብላቸው የጋበዙን መጣጥፍ ርዕስ ዓይኔን ሳበውና ጭብጡን ለማግኘት ስል ደጋግሜ ዘለቅኩት። የጓጓሁት በርዕሱ እንዳመለከቱን ስለ ኢትዮጵያዊነትና ስለ ኢትዮጵያዊ ሥነምግባር ሹክ የሚሉን ሃሳብ ይኖር ይሆን የሚል ጥያቄ ስላጫረብኝ ለዚሁ መልስ ልሻ ነበር።

አቶ ይልማ መጣጥፋቸውን የሚጀምሩት የኮሪያ ዘማች ስለነበሩት አጎታቸው ህልም ማለማቸውን በመናገር ነው። ሕልም በማየታቸውም ምክንያት የአጎታቸውን ስብዕና ትዝ ስላላቸው በጊዜው ነበር ብለው የሚመስክሩትን ኢትዮጵያዊ ሥነምግባር  ከአሁኑ ይዞታ ጋር በማወዳደር ያወሱናል። በሃሳብ ነጉደው  በዓይነ ሕሊናቸው ወደ ኋላ ተመልሰው በዚያን ዘመን የነበረውን የንጉሣዊ ሥርዓት ቃኝተው ሲያበቁ፤ ከዚያም ተከትሎ የመጣውን የደርግ ሥርዓትና የአሁኑን የኢህአዴግ መራሹ መንግሥት ሥርዓት በማወዳደር ሃሳባቸውን ይወረውራሉ። ካስነበቡን ሦስት ገጽ መጣጥፍ አንድ ተኩሉን ገጽ የያዘው የአጎታቸው ተሞክሮ ሲሆን በተለይም የኮሪያው ዘማች አጎታቸው እንዴት በገዛ እጃቸው ሰርተው እንደበለጸጉና በጊዜውእስከ ደርጉ ዘመን ድረስ "የፈረንጅ ቤት" በሚመስለው ቤታቸው

ተንደላቀው ሲኖሩ እንደነበሩ ካወሱን በኋላ በአሁኑ ዘመን ግን በኢትዮጵያ የሚታየውን ሥርዓተ አልበኝነት፤ሃይማኖት የለሽነት፤ሙስናና አጭበርባሪነት የወያኔ መንግሥት ያመጣው ማህበራዊ ችግር እንደሆነ ይነግሩናል። ለአባባላቸው እርግጠኛነት ሰሞኑን የከዱ ሁለት ቱባ የመንግሥት ባለሥልጣኖችና በሥነ ምግባር ጉድለት ምክንያት ተግሳጽ የደረሳቸውን አንድ ሌላ ከፍተኛ ባለሥልጣን ዋቤ ያቀርቡልናል። ከዚያም አያይዘው በአሁኑ ዘመን መሬት ለአልሚዎች በመሰጠቱ ምክንያት ለአቅመ ሔዋን ያልደረሱ የኦሮሞ ገብሬ ሴት ልጆች በአበባ እርሻ ውስጥ ለኬሚካል ተጋልጠው  እየሰሩ እንዳለ በቁጭት ይነግሩናል። በመጨረሻም በለገ ጣፎ አካባቢ እየተሰሩ ያሉት ዘማናዊ ቤቶች የሕዝቡን የመግዛት አቅም ያላገናዘቡ በመሆናቸው አጥብቀው ተቅውመው ሲያበቁ እነዚህን ዘመናዊ ቤቶች መሥራትም ሆነ የተሠሩትን መግዛት ከኢትዮጵያዊ ሥነምግባር ውጭ የሆነ ድርጊት ከመሆኑም በላይ ሀገርን መግደል ነው በለው ጽሑፋቸውን ይቋጫሉ።

የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ ተደራሲያኑ የሀገር ልጆች ስለሆኑ ከእንግሊዝኛው ይልቅ ብሔራዊ መግባቢያችን በሆነው በአማርኛ ቋንቋ ማፏጨት መርጦአል። በተጨማሪም አቶ ይልማ ባነሱአቸው ሦስት ሥርዓቶች  ያለፈ በመሆኑ ምስክርነቱን ለመስጠት ሞራላዊ ብቃት እንዳለው ልብ ይሏል።

አንደኛ፤ አቶ ይልማ ያነሱአቸው የኮሪያው ዘማች አጎታቸው ሀገራችንን ወክለው ለፈጸሙት ጀግንነት የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ ከመቀመጫው ብድግ በማለት ብሎ ባርኔጣውን አንሥቶ እጅ ይነሳል። ይሁንና ግን ከዘመቻ መልስ ከእኚህ ሰው ሰው ጋር አብረው የዘመቱት ጓደኞቻቸው እንደሌላው የሀገር ሰው ሁሉ በድህነት ሲማቅቁ እሳቸው ግን ተሳክቶላቸው

እጅግ ዘመናዊ ቤት ሠርተው ተንደላቅቀው ይኖሩ ነበር በመባሉ ሀብት ያፈሩበት ሁኔታ ያጠያይቃል። አቶ ይልማ ራሳቸው የዓይን ምሥክርነት ሊሰጡ እንደሚገደዱበት ሁሉ በዚያ ሥርዓት የነበረችው ኢትዮጵያ በንጉሣዊ አገዛዝ ሥር የነበረች የመልከኛ፤ ይጉልተኛና የገባር አገር ነበረች። ባይጋነን ከመቶው እጅ ዘጠናው የሀገሪቱ መሬት ንግሡን ጨምሮ በጣት በሚቆጠሩ መኳንንት ባለቤትነት እጅ ነበረች። በግምት ከመቶው እጅ ዘጠናው ኢትዮጵያዊ ከባርነት ያልተናነሰ የገባር ሕይወት የሚገፋ የበይ ተመልካች ነበር። ታዲያ አቶ ይልማ ሊንግሩን እንደሚሞክሩት ሕጋዊነት፤ ታማኝነትና በገዛ እጅ ሠርቶ የመበልጸግ ነጻነት እኔና አቶ ይልማ በተፈጠርንባት ኢትዮጵያ አልነበረም። የአቶ ይልማ አጎት አፈሩት የተባለው ንብረት የንጉሡ ባለሟሎች፤ባላባቶችና መልከኞች እንጂ የመንግሥት ሠራተኛ ሊያፈራው የሚችለው ንብረት አልነበረም።

ከጽሑፋቸው ተነስቼ አቶ ይልማ አፍቃሬ ዘውዳዊ አገዛዝ ናቸው ብል የምሳሳት አይመስለኝም። ዘውዳዊ ሥርዓትን መደገፋቸው ሰብአዊ መብታቸው መሆኑ ሲሆን ነገር ግን ምናልባት አልሰሙ እንደሆን ያ ሥርዓት ዳግም ላይመለስ ሞቶ መቀበሩን መረጃ ልሰጣቸው እወዳልሁ። አሁን ዘመኑ ብዙሃኑ ራሱን በራሱ የሚይስተዳድርበት፤የራሱን እድል ራሱ የሚወስንበትና ከሀገሪቱ ሀብት ድርሻውን የሚያገኝበት ሥርዓት እየገነባ እንደሚገኝ ልብ ሊሉ ይገባል።

ሁለተኛ፤ አቶ ይልማ መሬት ለአልሚዎች መስጠቱንና የገበሬው ልጆች በዚህ እርሻ ላይ ተቀጥረው መሥራታቸው ልክ አይደለም ብለው ይሞግታሉ። በለገ ጣፎ አካባቢ ቤቶችን መገንባትም ሆነ የተገነቡትን ቤቶች መዛት ከኢትዮጵያዊ ሥነምግባር ውጭ ነው ሲሉም

ይከራከራሉ። ባለፈው ጊዜ “መቼም መማር እውነትን ለመፈለግና ለማመዛዘን ነው የሚጠቅመው። ይህ ካልሆነ ግን አንድ ያገሬ ሰው ከሠላሳ ዓመታት በፊት እንዳለው ‘መማር ለማመዛዘን ካልጠቀም ፍሬ ዘርቶ ገለባ ማጨድ ነው’ እንዳለው ብጤ ነው በማለት “ባሕላዊ፤ሞርላዊና ሥነምግባራዊ ዕሴቶቻንን እንጠብቅ” በሚል ርዕስ ባወጣሁት መጣጥፌ ያልኩትን እዚህም ጋ መድገም እሻለሁ። እዚህ ጋ ለአቶ ይልማ ሁለት ጥያቄዎችን ለማንሳት እፈልጋለሁ። ለመሆኑ አቶ ይልማ ለኢትዮጵያ እድገት የትኛው ሥነምጣኔያዊ ንድፈ ሀሳብ ነው ተስማሚው ብለው የሚያምኑት? ለመሆኑ ሞራላዊ ሥነምግባርስ ይረዳቸዋል? እንዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ እርሳቸው በሚያፏጩበት እንግሊዝኛ ቋንቋ የተጻፉ የብዙ ሥነ ምጣኔያዊ ሊቃውንቶች ሥራዎች በቅርባቸው ስለሚገኙ በሚቀጥለው ጊዜ አሁን ሀገሪቱ እየተከተለችው ያለው ምጣኔያዊ ንድፈ ሃሳብ ለምን እንደማይሠራና እንደሚገልጹልንና ሌላ የበሰለ አማራጭ ንድፈ ሃሳብ ይዘው ብቅ እንደሚሉና እንደሚያወያዩን እጠብቃለሁ።

ሦስተኛ፤ አቶ ይልማ ሙስናን አስመልክቶ ያነሱአቸው ሃሳቦች ምንም እንኳን ተጨባጭ መረጃ ያልቀረበባቸው ቢሆንም ቅሉ፤ በኢትዮጵያ ውስጥ ከቶም ሙስና የለም የሚል እንካስላንቲያ ላቀርብ አይዳዳኝም። ነገር ግን አቶ ይልማ በሚያሞካሹት ዘውዳዊ ሥርዓት ውስጥ ሙስና የሥርዓቱ የተለመደ የሕይወት ዘይቤ ነበርና እጅ መንሻ መቀበል፤ ፍትሕን ማጣመምና ከሕግ በላይ መኖር

የሹመኞች ወግ እንደነበር አንድ ማለት እፈልጋለሁ። በድርጉም ዘመን ቢሆን ሕግ የተዳጠበትና ሹመኞች ልባቸው ያሻውን ሲያደርጉ የነበረበት ሥርዓት እንደነበር በውስጡ ያለፍን ሕያው ምስክሮች ነን። አሁን ሃገሪቱን እያስተዳደረ በሚገኘው የኢህአዴግ ዘመን ሙስና አንዱ ዋና የዕድገትና የፍትሃዊነት ጠላት ምሆኑ ታምኖበት የጸረ ሙስና ኮሚሽን ተቋቁሞ ረጅም የሚባል ርቀት የተጓዘና ብዙ የማይናቅ ሥራ መፈጸሙ አያጠያይቅም። በመሰረቱ ሙስና የኢትዮጵያ ብቻ ችግር ሳይሆን ሰለጠኑ የተባሉትን ሀገሮች ጭምር የሚያስጨንቅ ማበራዊ ችግር መሆኑን አቶ ይልማ ይጠፉቸዋል ብሎ መገመት ያዳግታል። ሙስና መንግሥት ብቻውን የሚወጣው ችግር ሳይሆን በሕብረተሰቡ ውስጥ ሥር ነቀል የአስተሳሰብ ለውጥን በማምጣት መቀነስ እንደሚቻል የዚህ ጽሁፍ አቅራቢ ያምናል። አቶ ይልማ በስም የጠቀሱአቸው ባለሥልጣኖች በሙስና ስለመጠርጠራቸው ከሀገሪቱ የሕግ ሥርዓት የተሰጠ ፍንጭ ስለሌለ በዚህ ጉዳይ ላይ ለመነጋገር መሞከር  ወደ ተራ ስም አጥፊነት ዝቅ ስለሚያደርግ ጸሐፊው አስተያየት ከመስጠት ራሱን ይገታል።

አራተኛ፤አቶ ይልማ በአበባ እርሻ ውስጥ ስለሚሠሩ እድሜአቸው ለአቅመ ሔዋን ያልደረሱ ለጋ የገበሬ ሴት ልጆች ያላቸውን ሥጋት ገልጸውልናል። እሳቸው የሚሉት ችግር በማስረጃ የተደገፈ ከሆነ የዚህ ጽሑፍ አቅራቢም ሥጋቱን ይጋራል። ሆኖም ግን በዚህ ጸሐፊ እምነት የኢትዮጵያ ሠራተኞች አዋጅ ለአቅመ አዳም/ሔዋን

ያልደርሱ ልጆችን በሥራ ማሰማራት በሕግ እንዲሚያስጠይቅ ስለሚደነግግ አድራጊዊን በሕግ የሚይስጠይቅ ጉዳይ ነው። አቶ ይልማ አለ የሚሉን ይህ ችግር ስለመኖሩ እርግጠኛ ከሆኑ ግን ለሀገሪቱ ሕግ በማቅረብ እንዲዳኝ ቢያደርጉ ለወገን ተቆርቋሪነታውን እውን ያደርገዋል። በተጨማሪም በእርሻው ውስጥ ጥቅም ላይ ውለዋል ይሚሉአቸውን ኬሚካሎችንም በተመለከተ ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ ቁጥጥር እንደሚደረግበትና ይህንንም ለማስፈጸም ብቃት ያላቸው ባለሙያዎች በሃገር ውስጥ እንድሉ ስለማያጠራጥር ሥጋቱ መሰረት ያለው አይመስልም።

በነገራችን ላይ አቶ ይልማ ስለሰብአዊ መብቶች ካነሱ አይቀር በደርጉ ዘመን አንድ ሚሊዮን ተኩል ኢትዮጵያውያንን ጨፍጭፈው ሲያበቁ አሁን ገን መኖሪያቸውን በምዕራባውያን አገር አድርገው በሳታላይት ትቪና ራዲዮ የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች ስልሆኑት ወንጀለኞች ትንፍሽ አለማለታቸው የተጨፈጨፉት ኢትዮጵያውን ቁጥር አንሶባቸው ይሆን አሰኝቶኛል? ወይስ በዚያ ዘመን በብሔራዊ ቲአትር “በ አብዮታዊው መሪ ፍሮው ጎመራ” ዘፈን በወንድሞቹና እህቶቹ ደም ላይ ቆሞ ዳንኪራ ሲረግጥ የነበረውን የደርጉን ታማኝ ስለማያውቁት ይሆን?

በመጨረሻም የጋራ የሆነችው አገራችን ለምታ ሕዝባችን ከድህነት ተላቅቆ እንድናይ ሁላችንም አዎንታዊ የሆን አስተዋጽኦ ልናድርግ የተገባ ሲሆን አቶ ይልማም ቢሆን ጭብጥ ከሌለው እንቶ ፈንቶ ተላቀው ሀገርናን ወገንን ሊጠቅም የሚችል ውኃ የሚያቁር ንድፈሃሳብ እንዲያስነብቡን እጠብቃለሁ።

ቸር እንሰንበት!

ጃለታ ነኝ ከካሊፎርኒያ